የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ሚያዝያ 1/2004

<u>**ግልፅ ደብዳቤ ለሚስተር ቢል ጌትስ**</u>

የቢል ጌትስና የወ/ሮ ሚሊንዳ ጌትስ አግልግሎት መሥራችና ሥራ አስኪያጅ
ሲአትል
<u>ሰሜን አሜሪካ</u>

ሚስተር ቢል ጌትስ

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢ..ፖ.እ.አ.ኮ) ይህንን ደብዳቤ ሲጽፍልዎ በኢትዮጵያ ስላደረጉት የሁለት ቀን ጉብኝት የቀረበ ጋዜጣዊ ዘገባን አስመልክቶ እውነት እንደሆነ በመገመት ነው። ይህ ካልሆነ ደግሞ በመለስ አገዛዝ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ያለው የዜና ተቋም/ኢዜእ/ የውሸት ፐሮፓጋንዳውን ሲያሰራጭ ይህ የመጀመሪያው አለመሆኑን የሚያመለክት ማረጋገጫ ይሆናል ማለት ነው።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በ1995 ዓ.ም. የተቋቋመ ለሰብአዊ መብት ጥበቃ የቆመ ድርጅት ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ የሰብአዊና ዴሚክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ እየታገለ ያለ ህዝባዊ ድርጅት ነው። (ድረ ገፃችንን www.socepp.com ይመልከቱ)። የሰብአዊ መብት ሁናቴ በኢትዮጵያ ለአመታት እየተበላሸ ያለ በመሆኑ ሀገር በቀልም ሆኑ አለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው ለሰብአዊ መብት መጠበቅ ተከራካሪ የሆኑ ድርጅቶች የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ጭምር ያወገዙትና በስፋት ያጋለጡት ነው። ሆኖም የኢትዮጵያ የዜና ተቋም ሲዘግብ፦

„ ቢል ጌትስ እንዳሉት ኢትዮጵያ እድገት ማሳየቷን እንደምትቀጥልበት ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ። በኢትዮጵያ በርከት ያሉ እድገቶች ይታያሉ። በማለት ተናግረው በመቀጠልም ይህ እድገት ግን መመዘን የሚኖርበት ከጤንነት፣ ከምግብ አቅርቦት፣ ከኑሮ ገቢ ጥቅም መገኘት አንፃር ነው።“ በማለት ለንባብ አቅርቦታል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ለእርሶ ለመግለፅ የሚፈልገው ይህ አስተያየት ከእውነቱና ከተጨባጭ ሁናቴው የራቀ መሆኑን ነው። የትግራይ ቡድን የሆነው የመለስ አገዛዝ ተሰሚነት ላላቸውና ይጠቅሙኛል ለሚላቸው ባዕዳኖች ጉብኝትን በማዘጋጀት ችሎታ ያለው፤ አጭበርባሪና የተሳሳቱ መረጃዎችን እንደልቡ የሚያምታታ ነው። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች አሁንም ድረስ በባዕዳን የምግብ እርዳታ ጥገኛ በሆኑበት፣ የገንዘብ ዋጋ መርከሱ ይበልጥ እያሽቆለቆለ ባለበት፣

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቤተሰቦች ለከፋ ችግር በተዳረጉበት፡ አዳዲሶቹ የትግራይ ቡድኖች በከፍተኛ ሙስና በተዘፈቁበት ሁናቴ በብዙሃኑ ሕዝብ በኑሮ ገቢ ላይ ምንም አይነት መሻሻል አልተገኘም። በቂ ምግብ የማግኘት ሁናቴ እንደ መመዘኛ ከተወሰደ ኢትዮጵያ ሕዝቦቿ እየተራቡ ሲሆኑ በአዲስ አበባ እንኳን መራብ ሊደበቅ የማይችል የቀን ተቀን ሀቅ ነው። የኑሮ ገቢ ጥቅም ማግኘት ዋና ርዕስ ከተደረገም ለአገዛዙ ቀና አመለካከት ያላቸው ባዕዳን ሀገሮችና ኤጀንሲዎች ሀብታም በሆኑ ኢሚንቶችና ያለምንም ርህራሄ ለከፋ ድህነት በተዳረጉ ብዙሃኖች መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት ባለፉት አመታት በጣም እየሰፋ የሄደ መሆኑን ለማመን ይገደዳሉ። ታዲያ ምን አይነት እድገት ነው በጤነንት መስክ የተመዘገበው? ከጤና ጥበቃ ሚኒስትሩና የበላይ ሹማምንተኞቹ ጋር ውይይት ከማድረግ ይልቅ ሕዝቡን ማነጋገሩ የተሻለ ነበር እንልዎታለን።

የተከበሩ ቢል ጌትስ

የኢትዮጵያ የዜና ተቋም እርስዎ ስለሰጡት ገለፃ ያቀረበው ዘገባ ትክክል ከሆነ የተሳሳተ ዘገባ ሰጥቶዎታልና በአፍሪካ በጨካኝ አምባገነንነቱ ለታወቀ፡ ከ35000 በላይ የሆኑ ዜጎችን በየጉድጓዱና ማጎሪያ እስር ቤቶች ውስጥ ለሚያፍን፡ በርካታዎች ከመቶ በላይ የሚሆኑ ደብዛቸውን ያጠፋ አሁንም በቀጣይነት የሕዝብን ሰብአዊ መብት ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን እየደፈጠጠ ላለ አገዛዝ ድጋፍ መስጠት ነው የሚሆነው። በምግብ ራስን የመቻል ግብ እንደሚሳካ ተስፋ ሊኖርዎች ይችል ይሆናል። ነገር ግን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ግን የተሳሳቱ መሆንዎን ሊነግሩዎት ይችላሉ።

የሕዝብ ጉስቁልና አስከፊነቱን ባለማየት ወይንም ወደጎን በማድረግ ነገር ግን ደግሞ በየቦታው ለሚሰሩ ግንቦች ከፍተኛ እሴት እንዳላቸው ተደርጎ ከግምት ውስጥ እንዲገቡ ካልተደረገ በስተቀር በመልካምነት የሚታይ ተግባር በኢትዮጵያ እየተከናወነ አይደለም። ማነው ለምሳሌ የነፃ ፕሬስ ዋና ጠላት? ማነው በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የዘር ማፅዳት ተግባር የሚያከናውነው? ማነው በጉዲፈቻ እየተመካኘ ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ዜጎቹን ለዘመናዊ ባርነት እየላከና እጓለምውታን ሕፃናትን እየሸጠ ያለ ማነው? መልሱ በአዲስ አበባ የተገናኙት እንግዳ ተቀባይዎ መለስ ዜናዊ ራሱ ነው።

የኢትዮጵያ የዜና ተቋም እንደዘገበው አገዙ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነት እንደሚጨነቅና እንደሚጠበብ እምነት እንዳለዎት ተገልጿል። መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን በማንናውም መስክ ወደ ጥፋት እንደከተታት፡ በተለይም በቦታው በቅርበት በሚገኘውና የሕዝቡን ችግር ይበልጥ እያባባሰ ለሚገነው በሚሊዮን የሚቆጠር የገንዘብ እርዳታ የሚለግሰው የእርሶ ድርጅት ይመለከተኛል በሚለው በጤንነት፡ በትምህርት መስክ ወደ ጥፋት ጎዳና እንደከተታት ይታያል።

በኢትዮጵያ እውነት እንደሬት ትመራለች፡ የመታነቂያ ገመድም በአንገት ውስጥ ታስጠልቃለች ይባላል። ይህንን ግልፅ ደብዳቤ በቀና ሊመለከቱት እንደማይችሉ ሁሉ የርሶ ድርጅት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዳልቆሙ ግን ሊያውቁት ይገባል። ሕዝብን እየረዱ አይደሉም። የሚለግሱት እርዳታ እነሱኑ ለሚጨቁናቸውና አምባገነን ለሆነ አገዛዝ ሲሆን የሱ ከሥልጣን መቆየት አለመቆየት የተመሰረተው በባዕዳን እርዳታ የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የመለስ አገዛዝ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ገድሏል፡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩትን ከቄያቸው አፈናቅሏል፡ የጎሳ

ልዩነትንና ጭቆናን አራምዷል፡ በጅምላ ግድያ ላይ ተሰማርቷል፡ ሰዎችን ለእስር ዳርጓል፤ ስልታዊ በሆነ ሁኔታና ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን ግብረስየልን ፈፅሟል፡ ሌላም፡ ሌላም።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ እርሶንና ድርጅትዎን ለአረመኔ የገንዘብ እርዳታ አይለግሱ ከአምባገነን ጋር መተቃቀፍና ብርጭቆ ማጋጨቱን አቁሙ በማለት መጠየቁ ተገቢም ግዴታም ነው።


INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE